# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ስር ለሚገኙ ህብረት ስራ ማህበራት

# የዕርቅ እና የሽምግልና ዳኝነት ለማየት የሚያስችል መመሪያ ቁጥር 99/2014

መጋቢት 2013

# መግቢያ

የህብረት ሥራ ማህበር ሰ ች በፍቃደኝነት ኢኮኖሚዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸዉን በጋራ ለመፍታት የሚያቋቁሙትና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚያስተዳድሩት ማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ድርጅት ነዉ ።

ህብረት ሥራ ማህበራት በሚያደርጉት የሥራ እንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ ህብረት ሥራ ማህበራት አባላት፤ ቀድሞ የህብረት ሥራ ማህበራት አባላት፣ ቅጥር ሰራተኞቻቸዉና የንግድ ልውውጥ ሚያካሂዱባቸው ድርጅቶች ወዘተ. ጋር አለመገባባቶች ሲገጥማቸው ይችላል። ህብረት ሥራ ማህበራት ጋር የሚነሱ አለመግባባቶች ዕርቅ ወይም በሽምግልና ዳኝነት እንዲታዩ በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 ከአንቀፅ 61 እስ 67 ተደንግጓል።

የህብረት ሥራ ማህበራት አለመግባባቶችን ለፍ/ቤት አቅርበው ረጅሙን የፍ/ብሔር ክርክር ሂደት ተ ትለው ለመ ራ ር የሚገጥማቸውን የገንዘብና የጊዜ እጥረት ለማቃለል ህብረት ሥራ ማህበራቱ እንቅስቃሴያቸውን ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ በማ ናወን ብክነትና ጥፋት ተጠብቀው ለአገሪቱ ልማት የሚያደርጉትን አስተዋፅኦ ፍ ለማድረግ ነው።

በመሆኑም የህብረት ሥራ ማህበራቱ ሕግን ጠብቀው የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማሳካት እንዲችሉ የሚገጥሟቸውን አለመግባባቶች በዕርቅ ወይም በሽምግልና ዳኝነት መፍታት የሚያስችላቸውን ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

በዚህ መሰረትም የህብረት ሥራ ማህበራትን ለማደራጀት፣ ለመመዝገብና ለመቆጣጠር እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም የተቋቋመው የአዲስ አበባ ህብረት ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 70/8/በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን የአሰራር ስርዓት ሠነድ አዘጋጅቷል።

# ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### የህብረት ሥራ ማህበራት የዕርቅና የሽምግልና ዳኝነት አፈጻፀም መመሪያ

## 1 አጭር ርዕስ
ይህ መመሪያ «በአዲስ አበባ በሚገኙ ህብረት ሥራ ማህበራት የሚነሱ ክርክሮችን በዕርቅና በሽምግልና የሚፈቱበት የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 99/2014 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ
የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉት ቃላቶችና ሐረጎች በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 ሲሆን በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ የተለያዩ ሀረጐች ወይም ቃላቶች የሚ ተለውን ትርጉም ይይዛል

### 2.1. ዕርቅ ማለት
በሁለት ተዋዋይ ወገኖች መካ ል (በፍ/ቤት የተያዙ ጉዳዮችንም ጭምር) በዕርቅ ፣ በድርድርና በተለያዩ ስምምነቶች አንዱ ወገን ሳንዱ አንድ ነገር ትቶ ወይም ሰጥቶያለባቸውን ችግር የሚፈቱበት ወይም የተጀመረዉን ክርክር የሚያቆሙበት ወይም የሚፈጠረዉን ክርክር አስቀድመዉ የሚያስቀሩበት አስገዳጅነት ያለዉ አንድ ዉል ነዉ ፡፡

### 2.2. የሽምግልና ዳኝነት ማለት
ሁለት ተ ራካሪች ጉዳያቸዉን መደበኛው ፍ/ቤት ውጭ በ ህብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 መሠረት ለሚመርጧቸው የሽምግልናዳኞች የስምምነት ዉል በማቅረብ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ መሠረት በማ ራ ር አስገዳጅ የሆነ ውሣኔ የሚሰጥበት ዳኝነት ነው

### 2.3. «አስታራቂች »ማለት
ተዋዋይ ወገኖች በመካ ላቸው ያለውን ክርክር ለመፍታት እንዲችሉ እንዲያስታርቋቸውና በመካ ላቸው ግልግል እንዲያደርጉላቸው በመምረጥ ሥልጣን የተሰጣቸው ሦስተኛ ወገን ናቸው፡፡

### 2.4. «የሽምግልና ዳኞች? ማለት
ተዋዋይ ወገኖች በመካ ላቸዉ ያለዉን ክርክር በህግ አግባብ መሰረት በሽምግልና ዳኝነት እንዲጨርሱላቸዉ በህብረት ሥራ አዋጅ መሰረት የሚመረጡ ሰ ች ማለት ነዉ፡፡

### 2.5. «የቀድሞ አባል» ማለት
በተለያዩ ምክንያቶች ህብረት ሥራ ማህበራት የተሰናበተ አባል ማለት ነዉ፡፡

# ክፍል ሁለት

## አለመግባባቶችን በዕርቅ ስለመፍታት

### 3. በዕርቅ የሚቀርቡ ጉዳዮች

3.1 ማንኛዉም የህብረት ሥራ ማህበር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3.3 ተጠቀሡት አካላት ጋር የሚያጋጥማቸውን አለመገባባት ወይም የ ርክር ጉዳዮች በዕርቅ በግልግል መፍታት ይችላል፡፡

3.2 በህብረት ሥራ አዋጅ ቁ.985/2009 በአንቀጽ 61 ላይ እንደተመለ ተው ክርክሮች ስሽምግልና ዳኝነት መቅረባቸው በፊት ተ ራካሪ ወገኖች በሚመርጧቸው ሦስተኛ ወገኖች በግልግል ማየት ይችላሉ፡፡

3.3 ዕርቁም የሚካሄደው በህብረት ሥራ ማህበራትና በሚ ተሉት አካላት ይሆናል፡፡

ሀ) በአባላት ወይም በቀድሞ አባላት ወይም የቀድሞ አባላት ስንብረታቸዉ በወ ኳቸዉ ወይም በሞት በተለዩ አባላት መብት ስም ክርክር በሚያቀርቡ ሰ ች መካ ል የሚነሳ ክርክሮችን፡-

ለ) በአባላቱ፣ በቀድሞ አባላት ወይም በአባላት ወይም በቀድሞ አባላት ወ ሎች ወይም በሞት በተለዩ አባላት ወራሾችና በህብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ አመራር ሚቴ በማናቸውም ሹም፣ በወ ሉ ወይም በህብረት ሥራ ማህበሩ ሠራተኛ መካ ል የሚነሣ ክርክሮችን፡-

ሐ) በህብረት ሥራ ማህበሩ ወይም በሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም በማናቸውም የቀድሞ የሥራ አመራር ኮሚቴ ማንኛዉም ሹም፣ ወ ል ወይም ሠራተኛ ወይም የቀድሞ ሹም፣ የቀድሞ ወ ል ወይም የቀድሞ ሠራተኛ ተጠሪው ፣ ወራሾቹ ወይም ወ ሎቹ ወይም በሞት በተለዩ የህብረት ሥራ ማህበሩ ሹሞች፣ ወይም ሠራተኞች መካ ል የሚነሳ ክርክሮችን፡-

መ) አግባብ ባለው ባለስልጣን በህብረት ሥራ አዋጅ መሠረት የተመዘገበ ሌላ ማህበር ወይም ማህበራት መካ ል የሚነሳ ክርክርና ህብረት ሥራ ማህበራት ጋር የንግድ ልውውጥ ሚያደርጉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ጋር የሚነሱ ክርክሮች ናቸው፡፡

### 4. የአስታራቂ- ች አመራረጥ

4.1 እያንዳንዱ ወገን አንድ አንድ ሰው አስታራቂ ይመርጣል፣

4.2 የአስታራቂች ሰብሳቢ የሚሆነው ሰው በሁለቱ ወገኖች በስምምነት ይመረጣል፤ የአስታራቂችም ቁጥር 3 ይሆናል፣

4.3 ሁለቱ ወገኖች ሰብሳቢ ለመምረጥ ስምምነት ላይ ያልደረሱ ሆነ ሰብሳቢው አግባብ ባለው አካል ይመረጣል፡፡

## 5. ስአስታራቂነት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች

5.1 ስአስታራቂነት የሚመረጡ ግስሰቦች በአካባቢው በመልካም ጠባያቸውና በጥሩ ሥነ ምግባራቸው የሚታወቁ መሆን አስባቸው፣

5.2 ስአስታራቂነት የሚመረጡት ሰ ች ቢያንስ ማንበብና መጻፍ አስባቸዉ፣

## 6. የዕርቅ አፈፃፀም

6.1 ዕርቅ በተዋዋዮች መካ ል የሚፈጠር ውል ነው፡፡ ስስዚህም በሕግ በየትኛውም የተደነገጉት የፎርም ግዴታዎች መጠበቅ አስባቸዉ፡፡

6.2 ዕርቅ በተ ራካሪ ወገኖች መካ ል ይግባኝ ሣይኖረው የመጨረሻ ሆኖ እንደተፈረደ ፍርድ የሚቆጠር ነዉ፡፡

6.3 ዕርቁ ስሕግ ወይም ስመልካም ተግባር ተቃራኒ ሆነ እንዲሁም ሌሳ ዉል ጋር ግንኙነት ያስው ሆነ ፈራሽ ነው፡፡

6.4 ተመሳሳይ ጉዳይ ባሳቸዉ ባስጉዳዮች በአንዱ የተደረገ ግልግል ሌሎቹን ባስጉዳዮች አያስገድድም እነርሱም መቃወሚያ ሲያደርጉት አይችሉም፡፡

## 7. ስዕርቅ የሚቀርቡ ባስጉዳዮች

7.1 ባስጉዳዮች በህግ ችሎታ ያሳቸው መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ክርክሩን በዕርቅ መጨረስ አይቻልም፣

7.1 ስዕርቅ የሚቀርበው ሰው /ድርጅት/ በቀጥታ ጉዳዩ የሚመስ ተው መሆን አስበት፡፡

## 8. በተገሳጋዮች መሟሳት ሰስሚገባቸዉ ጉዳዮች

ስዕርቅ በሚቀርቡ ባስጉዳዮች የሚ ተሉት ነጥቦች መሟሳት አስባቸው

8.1 ስዕርቁ ሲቀርቡ የሁስቱ ስምምነት በጽሁፍ መኖር አስበት፣

8.2 የክርክር አቀራረቡ የፍትሐ ብሔር ሕጉ በሚያዘዉ ፎርም መሠረት መሆን አስበት፡፡

## 9. የዕርቅ ስምምነት ስስሚይዛቸው ጉዳዮች፣

9.1 የተ ራካሪ ወገኖችን ስም፣ አድራሻ፣ (የመኖሪያ ቦታና ጥሪ ስመሳክ የሚያመች አድራሻ)

9.2 የዕርቁን ስምምነት የሚያመስክት የፍሬ ነገር መግስጫ፣ነገሩ በፍ/ቤት ተይዞ ሆነ፡-

ሀ) የቀረበበትን ፍ/ቤት ስምና አድራሻ፣

ስ) የክሱን አርዕስትና የመዝገቡን ቁጥር፣

ሐ) ተዋዋይ ወገኖች ስዉሳኔዉ የሚገዙ መሆናቸዉን ቃል በመግባት ይህንኑ በፊርማ ማረጋገጥ አስባቸዉ፡፡

## 10. በዕርቅ ስለሚሰጥ ዉሣኔ አዘገጃጀትና ይዘቱ

10.1 የሚሰጠው ዉሳኔ በፍ/ቤት እንደሚሰጥ የፍርድ ዉሣኔ ዓይነት ይዘጋጃል፣

10.2 የካሣንና የ ሣራን ጉዳይ ሲወስን ይችላል፣

10.3 የገላጋዮቹ ውሣኔ በድምፅ ብልጫ በሆነ ጊዜ አብላጫው ድምፅ የደገፈው ዉሳኔ የፀና ይሆናል፣

10.4 ዉሳኔዉ ቀንና ዓመተ ምህረት ተሞልቶበት በገላጋዮቹ ተፈርሞበት ስተዋዋይ ወገኖች አንዳንድ ግልባጭ ይሰጣቸዋል፣

## 11. ስለገላጋዮች አበል አወሳሰን

ስገላጋዮች የሚ ፈል አበል አይኖርም፡፡

## 12. በገላጋዮች የተሰጠውን ዉሳኔ ስለማስፈፀም

የዕርቅ ውሣኔ የተሰጠው ወገን በዉሣኔው መሠረት እንዲፈፀምለት ሲያመለክት ውሣኔው የሚፈፀመው በፍ/ቤት የተሰጠ ፍርድ በሚፈፀምበት ዓይነትና ሁኔታ ነው፡፡

## 13. የዕርቅ ስምምነትን ስለመመዝገብ

ክርክሩ በፍ/ቤት በመስማት ላይ ሆነ ተ ራካሪ ወገኖች ነገሩን በዕርቅ ስመጨረስ ስማቸውን ጽፈውና ፈርመው ጉዳዩን ስያዘው ፍርድ ቤት ማቅረብ አለባቸው፡፡

## 14. ተፈፃሚነት ያላቸው ህጎች

14.1 የህብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 985/2009

14.2 የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግና የፍ/ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ፣

14.3 የህብረት ሥራ አዋጅ ማስፈጸሚያ ደንብ

14.4 የህብረት ሥራ ማህበራትን ስማደራጀት ስመመዝገብና ስመቆጣጠር በህብረት ሥራ አዋጅ የተቋቋመ መስሪያ ቤት አግባብ ያስው ባለስልጣን የሚያወጣቸዉ መመሪያች፣

14.5 በተገላጋዮች መካ ል የተደረገው የስምምነት ሰነድ ስሁስቱ ወገኖች እንደ ሕግ ሆኖ ያገስግላል፡፡

14.6 የህብረት ስራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ

## 15. የገላጋዮች ተግባርና ሀላፊነት

15.1 ተገላጋዮች ጉዳያቸውን በትክክልና ያስ ምንም አድል እንዲያቀርቡና በእ ልነት እንዲ ራ ሩ ማድረግ፣

15.2 የዕርቅ ሥራዉን ስማካሄድ ተስማሚ የሆነ አካባቢ መምረጥና ተስማሚ ሁኔታዎችን መፍጠር፣

15.3 ስሚቀርቡት አስመግባባቶች ዉጤታማ መፍትሔ ስመስጠት የሚቻስውን ሁሉ ጥረት ማድረግ፣

15.4 ተገላጋዮች ጉዳያቸውን እንዲያስረዱ መፍቀድ፡፡

15.5 የመጨረሻ ውሣኔ መሰጠቱ በፊት ተገልጋይ ወገኖች አስተያየቸውን እንዲያቀርቡ መፍቀድ

15.6 በዕርቁ ሁስቱ ተገልጋዮች የደረሱበትን ውሣኔ በጽሑፍ መያዝ፣

15.7 ስማስታረቅ ካልተቻስ ዕርቅ አስመደረጉን በመግስጽ ቃስ-ጉባኤ ማዘጋጀት፣

15.8 የተዘጋጀውን የዕርቅ ስምምነት ወይም ዕርቅ አለመደረጉን የሚገልፀዉን ጽሑፍ ለተገላጋይ ወገኖች አዘጋጅተዉ መስጠት፡፡

15.9 የዕርቁ አፈጻጸም ሪፖርት አዘጋጅተዉ ተሰጠዉ የግልግል ዉሳኔ ጋር አያይዘዉ አግባብ ላለው ያቀርባሉ፡፡

15.10 ገላጋዮች አቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ካላጋጠማቸዉ በስተቀር ተመረጡበት ቀን ጀምሮ ቢበዛ በአንድ ወር ጊዜ ዉሰጥ የግልግል ስራዉን ይፈጽማሉ፡፡

## 16. በገላጋዮች የሚሰጥ ትዕዛዝ

በገላጋዮች የሚሰጠው የዕርቅ ዉሣኔ ተገላጋዮች ወይም ተዋዋዮች ያልተግባቡበትን ጉዳይ አይቶ በተቻለ መጠን ሁሉም ወገን ደረሰበት ሣሪ/ጉዳት/ እንዲካቀቅ መሆን አለበት፡፡ በዕርቁም የሚሰጡት ውሣኔ ች የሚ ተሉትን መያዝ አለባቸው፡፡

ሀ. የገንዘብ ክፍያ ውሣኔ ተሰጥቶ ሆነ ገንዘቡ እንዲ ፈል ትዕዛዝ መስጠት፣

ለ. በግልግሉ ውስጥ ስምምነት የተደረሰባቸው ጉዳዮች በአግባቡና በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲፈፀም ትዕዛዝ መስጠት፣

## 17. አግባብ ያለው ባለስልጣን ተግባርና ሀላፊነት

17.1 በተገላጋዮች መካ ል ያለን ጉዳይ በዕርቅ ለመጨረስ በዕርቅ ዉሳኔው ጣልቃ ሳይገባ ለሥራው ምቹ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

17.2 ተገላጋዮች ጉዳያቸውን በዕርቅ እንዲጨርሱ ሙያዊ የምክር አገልግሎት መስጠት፣

17.3 ተገላጋዮች የቀረበው የዕርቅ ስምምነት በህብረት ሥራ አዋጅ በተደነገገው መሠረት በተ ራካሪ ች ፍላጐትና ሙሉ እምነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማረጋገጥ፣

17.4 ለዕርቁ የቀረበው ጉዳይ ሕግ ጋር የማይጋጭና ሞራልን የማይነካ መሆኑን ማረጋገጥ፣

17.5 የገላጋዮች አመራረጥ የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ በሚፈቅደው መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፣

17.6 ተገላጋዮች ሰብሳቢ ለመምረጥ ስምምነት ላይ ካልደረሱ ሰብሳቢውን በአዋጅ ቁ.985/2009 አንቀፅ 63 መሠረት በመምረጥ ለሁለቱም ወገኖች ማሣወቅ፣

17.7 ተ ራካሪ ወገኖች ገላጋዮችን ለመምረጥ የእ ልነት መብት ማግኘታቸውንና ያለምንም ተጽዕኖ መሆኑን ማረጋገጥ፣

17.8 የተሰጠው ብይን ወይም ውሣኔ ተ ራካሪ ወገኖች ባቀረቡት የዕርቅ ስምምነትና በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ መሠረት መሆኑን ማረጋገጥ

17.9 ተገላጋይ ወገኖች ጉዳያቸውን ለማስረዳትና ክርክራቸውንም ቀርበው ለማሠማት በእ ልነት መብት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣

17.10 ገላጋዮች ያቀረቡት የዕርቅ ሃሣብ በተ ራካሪ ች ተቀባይነት ካላገኘ የተ ራካሪ ወገኖች የክርክር ጉዳዩና በገላጋዮች የተደረጉ የማጣራት ሂደቶች ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃ- ች በማያያዝ በ15 ቀናት ውስጥ በሽምግልና ዳኝነት እንዲታዩ ማድረግ፣

17.11 ለዕርቅ ስራዉ የሚዉል በጀት በተተመነዉ መሰረት ሁለቱም ወገኖች በሚወ ለዉ ሰዉ እጅ እንዲቀመጥ ማሠባሰብ፣ ክፍያዉም ቀደም ሲል በተወሰነዉ መሰረት መፈፀሙን መ ታተል፡፡

# ክፍል ሦስት
# ክርክሮችን በሽምግልና ዳኝነት ስለመጨረስ

## 18. ስለ ሽምግልና ዳኝነት

18.1 ሽምግልና ዳኝነት የሚፈጸመዉ ተ ራካሪ ወገኖች ያልተግባቡባቸውን ክርክሮች ለሽምግልና ዳኞች በማቅረብ በሚሰጠው ዉሣኔ ለመገዛት ስምምነት ላይ ደርሰው ሲቀርቡ ነው፣

18.2 የሽምግልና ዳኝነትን እንደ አንድ አስገዳጅ የአለመገባባቶች መፍቻ መፍትሔ መጠቀም የሚቻለው በህብረት ሥራ አዋጅ አንቀጽ 64 ላይ የተዘረዘሩትን ክርክሮች ለመፍታትና ህብረት ሥራ ማህበራት ጋር የንግድ እንቅስቃሴ ካላቸዉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ጋር የሚነሱ ክርክሮችን ለመፍታት ይሆናል፣

## 19. በሽምግልና ዳኝነት የሚታዩ ጉዳዮች

19.1 ማንኛውም የህብረት ሥራ ማህበር በዕርቅ ያልተፈቱ ክርክሮችን በሽምግልና ዳኝነት እንዲታዩ ያደርጋል፣

19.2 በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3.3 ላይ የተመለ ቱት ክርክሮች ለሽምግልና ዳኝነት መቅረባቸው በፊት በግልግል መታየት አለባቸው

## 20. ስለሽምግልና ዳኞች አመራረጥ፣

20.1 እያንዳንዱ ወገን አንድ የሽምግልና ዳኛ ይመርጣል፣

20.2 ለሽምግልና ዳኝነቱ ሰብሳቢ እንዲሆን የሚመረጠው ሦስተኛ ዳኛ በጋራ በሁለቱም ወገኖች ይመረጣል፣

20.3 የሽምግልና ዳኝነቱን ሰብሳቢ ለመምረጥ ሁለቱ ወገኖች ስምምነት ላይ ካልደረሱ ሰብሳቢው አግባብ ባለው ባለስልጣን ይመረጣል፣

## 21. ለሽምግልና ዳኝነት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች

21.1 ለሽምግልና ዳኝነት የሚመረጡ ሰ ች በአካባቢው ህብረተሰብ በመልካም ሥነ ሥርዓትናሥነ ምግባር የታወቁ መሆን አለባቸው፡፡

21.2 ለሽምግልና ዳኝነት የሚመረጡ ሰ ች ቢያንስ አንዱ የህግ ዕዉቀት ያለዉ ሆኖ ሁሉም ማንበብና መጻፍ አለባቸዉ፡፡

## 22. የሽምግልና ዳኝነት አፈፃፀም

22.1 የሽምግልና ዳኞች ክርክሮችን የሚሰሙትና የዳኝነት ተግባሩን የሚፈጽሙት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት ነው፡፡

22.2 በሽምግልና ዳኝነት የሚሰጥ ማንኛዉም ዉሣኔ፣ ትዕዛዝ ወይም ብይን በፍትሐ-ብሔር ችሎት እንደተሰጠ ተቆጥሮ አስፈላጊ ሲሆን ፍ/ቤቶች ውሣኔዉን፣ ትዕዘዙን ወይም ብይኑን እንዲፈፀም የማስገደድ ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡

## 23. የሽምግልና ዳኞች የፍትሐ ብሔር ሥልጣን

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3.3 የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ስማ ራ ርና ዉሣኔ ለመስጠት የሽምግልና ዳኞች የፍትሐብሔር ችሎት ሥልጣን አላቸው::

በዚህ መሠረት:-

23.1 ምስክሮችን የመጥራት፣

23.2 ለክርክሩ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃችን የማስቀረብ፣

23.3 ትዕዛዝ የመስጠት፣

23.4 ማንኛውንም ሕጋዊ እርምጃ የመውሰድ::

## 24. በሽምግልና ዳኝነት የተሰጠው ውሣኔ ስለሚፈፀምበት ሁኔታ

24.1 ፍርድ ቤቶች በህብረት ሥራ አዋጅ የሚሰጠውን ማንኛውንም ዉሣኔ፤ትዕዛዝ፤ ወይም ብይን በፍትሐ ብሔር ችሎት እንደተሰጠ በመቁጠር ውሣኔው፣ ትዕዛዙ ወይም ብይኑ እንዲፈፀም የማስገደድ ሥልጣን አላቸው::

24.2 የህብረት ሥራ ማህበራትን ለማደራጀትና ለማስፋፋት የተቋቋሙ አግባብ ያላቸው ባለስልጣናት በህብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 በተሰጣቸዉ ሥልጣን መሠረት አግባብ ላለው ፍ/ቤት በማቅረብ የተሰጠውን ዉሣኔ፣ትዕዛዝ ወይም ብይን በሥራ ላይ እንዲውል ወይም ተፈፃሚነት እንዲያገኝ ያደርጋሉ::

## 25. ስለ ይግባኝ አጠያየቅ

25.1 በሽምግልና ዳኝነት በተሰጡ ውሣኔች፣ትዕዛዝ ወይም ብይን ላይ ሁለቱ ወይም ሁለቱ አንዱ በህግ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ፣

25.2 ተ ራካሪው ህብረት ሥራ ማህበር ተጠሪነቱ ለፌዴራል መንግሥቱ በሆነ ተማ የሚገኝ ሆነ ተጐድቻለሁ የሚለው ወገን ለፌዴራል ፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀርባል::

25.3 ተ ራካሪው ህብረት ሥራ ማህበር በክልል የሚገኝ ሆነ ተጐጂ ነኝ የሚለው አካል ይግባኙን ለክልል ፍተኛ ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል፣

25.4 በሁለት ክልሎች ዉስጥ በተደራጁ የ ህብረት ሥራ ማህበራት መካ ል የሚፈጠር ክርክር ሆነ መጀመሪያው ሽምግልናዉ የሚታየው በፌዴራል ደረጃ በመሆኑ ይግባኙ የሚቀርበው ለፌዴራል ፍተኛ ፍ/ቤት ይሆናል::

## 26. የተ ራካሪ ወገኖች ግዴታ ች

26.1 ተ ራካሪ ወገኖች ለሽምግልና ዳኝነቱ ሥራ የሚሆኑትን መረጃች ለሽምግልና ዳኞቹ የማቅረብ ግዴታአለባቸው፣

26.2 የሽምግልና ዳኝነቱን ሥራ ሚያደናቅፍ ወይም በጣም አስቸጋሪ ሚያደርጉ ተግባራት መራቅ አለባቸው፣

26.3 ተ ራካሪ ወገኖች የሽምግልና ዳኞች ውሣኔ ስለ አለመደረጉ አንድ መግለጫ ካላቀረቡ በስተቀር የክርክሩ ጊዜ ማለቁ በፊት ክርክራቸውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ አይችሉም፡፡

## 27. <u>የሽምግልና ዳኞች ተግባርና ሀላፊነት</u>

27.1 የሽምግልና ዳኞች ሀላፊነት ለክርክር የሚቀርቡ የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት መዳኘትና ፍትህ መስጠት፣

27.2 የሽምግልና ዳኞች የመጨረሻ ውሣኔችን መግለፃቸው በፊት ለተ ራካሪ ወገኖች አስተያየታቸውን እንዲያቀርቡ መፍቀድ አለባቸው፣

27.3 የሽምግልና ዳኞች የውሣኔ ቃሎችን በጽሑፍ ማስፈር አለባቸው፣

27.4 ለሽምግልና ዳኝነት በቀረበው ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠት ካልተቻለ ይኸው ተጠቅሶ ስለጉዳዩ አንድ መግለጫ መዘጋጀት አለበት፣

27.5 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3ና4 ላይ የተገለፁት ጽሑፎች ለተ ራካሪ ወገኖች እንዲሁም ስራዉን አግባብ ላለው ባለስልጣን መስጠት አለባቸው፣

27.6 የሽምግልና ዳኞች (በሌላ አ ኗን ካልተወሰነ በስተቀር) ተመረጡበት ቀን አንስቶ ቢበዛ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ የሽምግልና ዳኝነት ተግባሩን መፈፀም አለባቸው፡፡

27.7 የሽምግልና ዳኞች ተሰጣቸዉ ተግባር እና ሀላፊነት ዉጭ ፈጽመዉ ቢገኙ አግባብ ባለዉ የአገሪቱ ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

## 28. <u>ለሽምግልና ዳኝነት ስለሚቀርቡ ባለጉዳዮች</u>

28.1 ባለጉዳዮች ሕጋዊ ችሎታ ያላቸው መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ክርክሩን በሽምግልና ዳኝነት ለማየት አይቻልም፣

28.2 በሽምግልና ዳኝነት ጉዳዩ እንዲታይለት የሚቀርበው ሰዉ በቀጥታ ጉዳዩ የሚመለ ተው ወይም ሕጋዊ ወ ል መሆን አለበት፡፡

## 29. <u>በተ ራካሪች መሟላት ስለሚገባቸዉ ጉዳዮች</u>

ለሽምግልና ዳኝነት የሚቀርቡ ባለጉዳዮች የሚ ተሉትን ማሟላት አለባቸው፣

29.1 በሽምግልና ዳኝነቱ ጉዳያቸውን ለመጨረስ ሲቀርቡ የተ ራካሪ ወገኖች ስምምነት መኖር አለበት፣

29.2 ክርክሩ የፍትሐብሔር ሕጉ በሚያዘው የክርክር ማቅረቢያ ፎርም መሠረት መቅረብ አለበት፡፡

## 30. <u>የሽምግልና ዳኝነት ስምምነት ስለሚይዛቸው ጉዳዮች፡-</u>

30.1 የተ ራካሪ ወገኖች ስም፣ አድራሻ (የመኖሪያ ቦታና ጥሪ ለመላክ የሚያመች አድራሻ፣)

30.2 ለሽምግልና ዳኝነቱ የቀረበዉን ጉዳይ የሚመለ ት የፍሬ ነገር መግለጫ፣ ነገሩ በፍ/ቤት ተይዞ ሆነ፡-

30.3 የቀረበበት ፍ/ቤት ስምና አድራሻ፣

30.4 የክሱን አርዕስት የመዝገቡ ቁጥር፣በትክክል ተጽፎ መቅረብ አለበት፡፡

## 31. <u>በሽምግልና ዳኝነት ስለሚሰጥ ውሣኔ ወይም ብይን አዘገጃጀትና ይዘቱ</u>

31.1 በሽምግልና ዳኝነት የሚሰጠው ውሣኔ ወይም ብይን በፍ/ቤት እንደሚሰጥ የፍርድ ውሣኔ ዓይነት ሆኖ ይዘጋጃል፣

31.2 የካሣና የ ሣራን ጉዳይ ሊወሰን ይችላል፣

31.3 የሽምግልግና ዳኞቹ ዉሣኔ በድምፅ ብልጫ በሆነ ጊዜ አብላጫው ድምፅ የደገፈው ብይን የፀና ይሆናል፣

31.4 ብይኑም ቀንና ዓመተ ምህረት ተሞልቶበት በሽምግልና ዳኞቹ ተፈረመበት በኋላ ለተዋዋይ ወገኖች አንዳንድ ግልባጭ ይሰጣቸዋል፡፡ የዉሳኔ መዝገቡም በአደራጅ መስሪያ ቤቱ ይቀመጣል፡፡

## 32. በሽምግልና ለመዳኘት በተ ራካሪ ች የቀረበውን ስምምነት ስለመመዝገብ

ተ ራካሪች ለሽምግልና ዳኝነት ያቀረቡት ጉዳይ ክርክሩ በፍ/ቤት መሰጠት ላይ ሆነ ተ ራካሪ ወገኖች ነገሩን በሽምግልና ዳኝነት ለመጨረስ መስማማታቸውን ጽፈውና ፈርመው ጉዳዩን ስያዘው ፍርድ ቤት ማቅረብ አለባቸው

## 33. በሽምግልና ዳኝነት ተፈፃሚነት ያላቸው ሕጐች

33.1 የህብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 985/2009

33.2 የኢትዮጵያ የፍትሀ ብሔር ሕግና የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ፣

33.3 የህብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 ለማስፈፀም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣ ደንብ

33.4 የህብረት ሥራ ማህበራትን ለማደራጀት፣ ለመመዝገብና ለመቆጣጠር በአዋጅ የተቋቋመ መ/ቤት የሚያወጣቸው መመሪያች፣

33.5 በተ ራካሪ ወገኖች መካ ል የተደረገው የስምምነት ሰነድ እንደ ሕግ ሆኖ ያገለግላል፣

## 34. የአደራጅ መ/ቤት ተግባርና ሀላፊነት

34.1 በተ ራካሪች መካ ል ያለውን ጉዳይ በሽምግልና ዳኝነት እንዲያልቅ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

34.2 ተ ራካሪች ጉዳያቸውን በሽምግልና ዳኝነት እንዲጨርሱ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

34.3 ለሽምግልና ዳኝነቱ የቀረበው ጉዳይ ሕግ ጋር የማይጋጭና ሞራልን የማይነካ መሆኑን ያረጋግጣል፣

34.4 የሽምግልና ዳኞች አመራረጥ የህብረት ሥራ አዋጅ በሚፈቅደው መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፣

34.5 ተ ራካሪች የሽምግልና ዳኞችን ሰብሳቢ ለመምረጥ ስምምነት ላይ ካልደረሱ ሰብሳቢውን ይመርጣል፣

34.6 ተ ራካሪ ወገኖች የሽምግልና ዳኞችን ለመምረጥ የእ ልነት መብት ማግኘታቸውንና ያለምንም ተፅዕኖ መሆኑን ያረጋግጣል፣

34.7 የተሰጠው ውሣኔ ወይም ብይን ተ ራካሪ ወገኖች ባቀረቡት ፍሬ ነገር መሠረትና በህብረት ሥራ አዋጅ ላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ መሆኑን ያረጋግጣል፣

34.8 ተ ራካሪ ወገኖች በክርክር ላይ ጉዳያቸውን ለማስረዳትና ክርክራቸውንም ቀርበው ለማሠማት በእ ልነት መብት ማግኘታቸዉን ያረጋግጣል፡፡

## 35. <u>የሽምግልና ዳኞች ወጪ ችና የድካም ዋጋ</u>

35.1 የሽምግልና ዳኞች ስሥራው አፈጻጸም ሲባል በተገቢዉ መንገድ የተፈፀሙ ወጪ ች ተመላሽ እንዲደረጉላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው፣

35.2 ሌላ ስምምነት ሌስ በቀር የሥራ ዋጋ ስማግኘት መብት የላቸውም

## 36. <u>ስስመመሪያው አጠቃቀም</u>

ይህ መመሪያ የህብረት ሥራ ማህበራትን ስማደራጀት ስመመዝገብና ስመቆጣጠር በህብረት ሥራ አዋጅ በተቋቋሙ መ/ቤቶች በሥራ ላይ ይዉላል፡፡

## 37 <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ መጋቢት ወር 2013 ዓ.ም. ጀምሮ በተግባር ይውላል፡፡

**የአዲስ አበባ ህብረት ሥራ ኤጀንሲ**

**ውብነህ እምሩ**

የአዲስ አበባ ህብረት ስራ ኤጀንሲ

ዳይሬክተር